በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከሴፕቴምበር 21-30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም ከኦክቶበር 1-10 እና ከኦክቶበር 11-20 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ከኦክቶበር 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምብር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ....- 1 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 4 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት....- 4 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምብር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 4 -
እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 5 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....- 5 -
እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 6 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 6 -
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ....- 7 -
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....- 8 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን....- 8 -
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 9 -
ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 9 -
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 10 -
እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 10 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምብር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት የሴፕቴምበር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በምዕራብ አጋማሽ፣ በመካከለኛዉ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጠናክረዉ ተስተውለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ዝናቡ ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ በመቀነስ የክረምቱን ዝናብ ሲያገኙ በቆዩት በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ጥንካሬ የነበረው ሲሆን፤ እንዲሁም ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ገጽታዎች ቀሰ በቀስ ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ከማፈግፈጋቸው ጋር ተያያዘ በዚህ ወቅት ዝናብ ማግኘት የሚጀምሩትን የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎችን ጨምሮ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው፡፡ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በሀዋሳ 63.0፣ በደብረ ማርቆስ 42.2፣ በነቀምቴ 34.3 እና 36.0፣ በአቦቦ 30.4፣ በአለምከተማ 32.2፣ በአለም ተፈሪ 52.4፣ በአማን 34.9፣ በአንገር ጉትን 35.4፣ በአርጆ 32.8 እና 42.6፣ በበደሌ 36.6 እና 38.4፣ በቻግኒ 32.8፣ በገለምሶ 43.0፣ በጊምቢ 32.9፣ በጉንዶ መስቀል 30.0፣ በሊሙ ገነት 54.2፣ በመተማ 40.4፣ በሠርቆሌ 36.0፣ በጠርቻ 37.6፣ በሂርና 46.0፣ በጨለንቆ 35.0 እንዲሁም በካራሚሌ 34.6 የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ21 የተለያዩ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለው የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-63 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል በሀዋሳ፣ በደብረ ማርቆስ፣ በአለም ተፈሪ፣ በአርጆ፣ በገለምሶ፣ በሂርና፣ በሊሙ ገነት እንዲሁም በመተማ ይጠቀሳሉ (ምስል 1)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፣ የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ የደቡብ፣ የማዕከላዊና የሰሜን ጎንደር፣ የአዊ ዞን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ጎጃም እና የደቡብ ወሎ ምዕራባዊው ክፍል፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፣ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሃረርጌ ዞኖች፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ እንዲሁም ቦረናና ምስራቅ ቦረና፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና የየም ልዩ ዞን እና ሀላባ ዞን፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ እና ባስኬቶ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከሶማሌ የሲቲና ፋፈን ዞኖች፣ አዲስ አበባ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ16-150 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከትግራይ የመካከለኛው፣ የምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ዞኖች፣ ከአማራ የደቡብ ወሎ ምስራቃዊው ክፍል፣ ሰሜን ወሎ እና ዋግህምራ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ፣ አውሲ፣ ማሂ፣ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች እንዲሁም ከሶማሌ የኤረር፣ ነጎብ፣ ጃረር የቆራሂ፣ የሸበል፣ የዶሎ፣ የአፍዴር፣ የሊበንና እና የዳዋ ዞኖች ላይ ከ6-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ3 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2)፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የሰሜን ምዕራብና የምዕራብ ትግራይ፤ የምስራቅና ምዕራብ አማራ፤ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የጋምቤላ ክልል የምዕራብ፣ የመካከለኛውና የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የተመዘገበ ሲሆን፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ፣ አውሲ፣ ማሂ፣ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምብር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በምዕራብ አጋማሽ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ባሉት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንዲሁም እርጥበቱ በዚህ ወቅት ከምስራቅ እና ከሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ ቀስ በቀስ የቀነሰ ቢሆንም በምስራቅ እና አጎራባች በሆኑ የአፋር አካባቢዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለው እርጥበት በማግኘታቸው ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተሻለ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበረ፡፡ ባለፉት የክረምት ወራት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅ በነበሩትና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አካባቢዎች የተገኘው እርጥበት ለሚካሄደው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና እንደነበረው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና ነበረው (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ መረብጋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞግቤ፣ ገናሌ ዳዋና፣ የታችኛውና የመካከለኛው ተከዜ፣ የላይኛው አዋሽ፣ እንዲሁም የላይኛው የዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል፡፡ የነበረው የእርጥበት ሁኔታም የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር የውሃ ሃብት ግብዓትን ከማሻሻልም በተጨማሪ ወደ ግልገል ጊቤ1 እና 2፣ ባሮ፣ ፊንጫ፣ ጣና በለስ እንዲሁም ቆቃ ግድቦችና የውሃ ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከማጎልበት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በአንፃሩም የክረምቱ ዝናብ ወደ ደቡብ፣ ምዕራብና መካከለኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ማፈግፈጉን ተከትሎ በአንዳንድ የምስራቅና ሰሜን ምስራቅ በሚገኙት የአፋር ደናክል፣ የአዋሽና፣ የላይኛው ተከዜ እንዲሁም ጥቂት የላይኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው እቀነሰ መሄዱን ያመላክታል(ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት የክረምት ድንበር ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሚያገኙ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

በመጪዎቹ የኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአብዛኛው በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረናና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የጀመረው የክረምት ወቅት ዝናብ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ጋር ተያይዞ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ በጥቂት ስፍራዎች ላይ ከባድ ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ምዕራብ፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና ማዣንግ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ እና የምዕራብ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ አዲስ አበባ፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ፣ ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ የቀበና፣ የጠምባሮ እና የማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ እንዲሁም የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ወላይታ፣ ኮንሶ፣ አማሮ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን፣ ሲቲ፣ ኤረር፣ ጀረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን፣ ቆራሂ  እና ዶሎ ዞኖች፤ እንዲሁም ሀረሪ እና ድሬዳዋ ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ በተጨማሪም በወለጋና በደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች፤ ጋምቤላ፤ በደቡብ ምዕራብ  እና በምስራቅ አከባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከኦሮሚያ ክልል ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ ከአፋር ክልል አዉሲ፣ ፋንቲ፤ ሃሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ዋህግምራ ዞኖች፤ ከትግራይ የደቡብ እና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ዳዋ፣ ሊበን እና አፍዴር ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10, 2024
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10, 2024
የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር ሁለተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛው በደቡብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8) ፡፡ በተጨማሪም በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በአንዳንድ የምዕራብና የደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8) ፡፡

Total Rainfall (mm) 11-20,Oct 2024




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ አስር ቀናት የሚጠበቀው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በማፍራት ላይ ለሚገኙ፣ በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና ዕድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፤ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በክረምት ወቅት መጨረሻ በአፈር ውስጥ በተከማቸው እርጥበት በመታገዝ በደጋማው አካባቢ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን የውሃ አቅርቦት ከማሟላት አንፃር አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

በተጨማሪም በዚህ ጊዜ የሚገኘዉ እርጥበት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ እንደሚኖረው ይጠበቃል። በተጨማሪም ውሃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር መጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የሰሜን አጋማሽ የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት አብዛኛዎቹ ተፋሰሶች የእርጥበት ሁኔታው በመጠንም ሆነ በስርጭት እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በሌላ በኩል ግን በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ የታችኛውና የመካከለኛው አባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው አዋሽ፣ እንዲሁም የላይኛው ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት ያለው እርጥበት እነደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህ ሁኔታ የከርሰ ምድር እና የገፀ ምድር የውኃ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et